የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No.15
ADDIS ABABA 24th, January, 2025

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፷፫/፪ሺ፲፯

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ማፍረሻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ…………………………………………………..………….………….ገጽ ፲፯ሺ፮፻፳፪

Content

Regulation No. 563/2025

Public Enterprises Holding and Administration Dissolution Council of Ministers Regulation ……………………………………….......Page 17622

ደንብ ቁጥር ፭፻፷፫/፪ሺ፲፯

<u>የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደርን ለማፍረስ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፭ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ማፍረሻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፷፫/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ስለመፍረስ</u>

በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ ተቋቁሞ የነበረው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር በዚህ ደንብ ፈርሷል፡፡

REGULATION No. 563/2025

<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE DISSOLUTION OF PUBLIC ENETERPRISES HOLDING AND ADMINISTRATION</u>

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.1263/2021.

1. <u>Short Title</u>

This Regulation may be cited as the "Public Enterprises Holding and Administration Dissolution Council of Ministers Regulation No.563/2025".

2. <u>Dissolution</u>

Public Enterprises Holding and Administration established by Proclamation No.1263/2021 is hereby dissolved by this Regulation.

፫. **<u>ስለመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለዕዳ እና የሀብት አስተዳደር ኮርፖሬሽን ተላልፈዋል፡፡

፬. **<u>የተሻረ ሕግ</u>**

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲን ተግባርና ኃላፊነትን ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፭/፪ሺ፲፩ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፭. **<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ጥር ፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፯

አብይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3. **<u>Transfer of Rights and Obligations</u>**

The Rights and Obligations of Public Enterprises Holding and Administration are hereby transferred to Liability and Asset Management Corporation.

4. **<u>Repealed Law</u>**

Definition of Powers and Duties of the Public Enterprises Holding and Administration Agency Regulation No.445/2019 is hereby repealed by this Regulation.

5. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force from January 14th day 2025 on which it was approved by the Council of Ministers.

Done at Addis Ababa, this 24th day of January, 2025

ABIY AHMED (DR)

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA